በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia
Ethiopian Revenues and Customs Authority


3.1-0/665/08
4 መጋቢት 2008

ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ኦርጅናልና ኦርጅናል ያልሆኑ መለዋወጫዎችን ይመለከታል</u>

ከተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያዩ ወቅት የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች Original እና non Original ብሎ ለመለየት አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት ወጥ የሆነ አሠራር ለመስራት መቸገራቸውን በደብዳቤ ገልፀውልናል፡፡

በመሆኑም በአዲሱ የዋጋ ትመና መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀጽ 25/2/ቀ/መሰረት የተሽከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች ዋጋ ለመተመን መሟላት ስለሚገባቸው መረጃዎች በተደነገገው መሰረት፡፡

1. የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃው የተሽከርካሪ መለዋዋጫው የሚገጠምበትን ተሽከርካሪ ባመረተው አምራች ኩባንያ በራሱ የተመረተ ወይም ከተሽከርካሪ አምራች ኩባንያ ጋር ባላቸው ውል በተሽከርካሪ አምራች ኩባንያው መስፈርት መሠረት በሌሎች የተሽከርካሪ መለዋዋጫ አምራች ኩባንያዎች የተመረተ ከሆነ እና በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ የተሽከርካሪ አምራች ኩባንያው ስም፣አርማ ወይም የንግድ ምልክት የሰፈረበት ከሆነ እንደ ኦርጅናል ተቆጥሮ በዚህ መሠረት ይስተናገዳል፡፡
2. የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃው ፣መለዋዋጫው የሚገጠምበትን ተሽከርካሪ ባመረተው አምራች ኩባንያ ያልተመረተ ከሆነ እና በዕቃው ወይም በማሸጊያው ላይ ኦርጅናል ያልሆነ የተሽከርካሪ መለዋዋጫ አምራች ኩባንያ ስም ፣አርማ እና የንግድ ምልክት የተገለጸበት ከሆነ መለዋወጫው ኦርጅናል ያልሆነ የተሽከርካሪ መለዋወጫ እንደሆነ ተቆጥሮ በዚሁ መሠረት ይስተናገዳል፡፡ ዕቃው ወይም መለዋወጫው አምራች ካልሆነ የንግድ ድርጅት ወይም ሶስተኛ ወገን የመጣ እንደሆነ ዕቃው ኦርጅናል አለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃው፣ በማሸጊያው ወይም በሰነዶች ላይ የኦርጅናል እና ኦርጅናል ያልሆነ የአምራች ስም፣ አርማ እና የንግድ ምልክት ተቀላቅሎ የተገለጸ ከሆነ፣ እንዲሁም በእቃው ወይም በማሸጊያው ላይ ምንም ዓይነት የአምራች ስም፣ አርማ እና የንግድ ምልክት ያልተገለፀ እንደሆነ እንደ ኦርጅናል ተቆጥሮ ይስተናገዳል፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>ግልባጭ</u>

- ለጉምሩክ ኘሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለታሪፍ ምዳባ አ/ኘ/ል ቡድን
- ለዋጋ ትመና አ/ኘ/ል ቡድን
- ለዋጋ መረጃ ዝግጅትና አጠቃቀም ጥናት ቡድን

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>